# መግባት ምኑ ገዶ!!!!!

(ከተስፋዬ)

መግባትስ ይግባ፣ ግን መግቢያችሁ ስልቱ፣
እንደ ፋኖው ጋይም፣ ቆርጦ በህይወቱ፣
በራስ መፍረድ መርጦ፣ እጅ ከመስጠቱ
ነው ጥሎ ለመውደቅ፣ ጀግና ክብር ሞቱ?
ወይስ ተስሞ ነው፣ ወያኔ ጉልበቱ?
ልትታጎሩለት፣ ከዚያው ከበረቱ?

በአመፅ ካልሆነ፣ በራፉን ደርምሶ፣
ቃሊቲ ደዴሳን፣ ሁሉን አፈራርሶ፣
የጠላትን እግር፣ ልሶ ተለሳልሶ፣
ለመግባት የእንብርክክ፣ አንገት ተጎንብሶ?
ጠይቆ ይቅርታ? ራስን አዋርዶ?
በአፊዴቪት ፊርማ፣ ልመና ተማልዶ?
መግባት ለፈለገ፣ መግባት ምኑ ገዶ!

ንጥር የሚረጨው፣ ሲሚጠጥ ሃሞቱ፣
የጀግናን ማርከሻ፣ ጋይምን ማንሳቱ፣
ቃጤ አሻሮ ይዞ፣ ማሳ ጤፍ ነው ጠጋ፣
በምህረት ለመግባት፣ በሰበብ ፍለጋ!!!!!
ማለፉ ለማይቀር፣ ይህ ጥቁር ደመና፣
ታሪክ አቆሽሾ፣ ወዴት ቀና ቀና፣
ያዕዕላፋት አደራ፣ ለማስቀረት መና፣
እንደሆነ ስናውቅ፣ ወና ማለት ባዶ፣ ባዶ ማለት ወና!